# የኣንጃ ጉባኤ-- የወያኔ መስመር ውድቀት

ባለፈው ሰሞን ከኢህአፓ የተገነጠለው አንጃ ጉባኤ አደረግኩ ብሎ ነበር። የአንጃው 45 አባላት ከአሜሪካና ሌሎችም አህጉራት በሞላ መጥተው ነበር። ቀደም ሲል ልዩ ልዩ ወረቀቶች ወርደው አባል የተባሉት የደረሳቸው ሲሆን አንጃው የከተማ ትጥቅ ትግል ያዋጣል የሚለውን ረቂቅ ግን በምስጢር ይዞ አቀይትዋል።

አንጃው በአዛውንቱ መርሻ ዮሴፍ መሪነት የኮበለለው ለወያኔ ሰነድ ፈርመንና የወያኔን መንግስትነት ተቀብለን እንግባ የሚል ስለነበርና መርሻና ጭፍሮቹም በዚሁ ስብሰባ ይህንን ለማስወሰን አቅደው የመጡ ስለነበር ዋናው የጭቅጭቅ ጉዳይም ይህ በመሆኑ የመርሻ ሎሌ አቡኔ ወደ ወያኔ እንግባ ብሎ ያቀረበው ሰነድ ይጸድቃል ተብሎ ነበር። ወደ ወያኔ እንግባ በሚል ተገንጥለናልና እንግባ ብለው በየነ ጉራና ዮህንስ ሲከራከሩ የዚሁ ኣቅዋም ዋናው አፈቀላጤ መርሻ ዮሴፍ ግን በተለመደው አድርባይነት የብዙዎቹን አዝማሚያ ካደመጠ በህዋላ የሁለገብ ትግል ደጋፊ ሆኖ ተከራከረ። ተከተል አለቃህን ነውናም ከሰላማዊ ትግል ሌላ ምንም አማራጭ የለም ይሉ የነበሩ እነ መስፍን ማርዮም ሳይቀሩ የሁለገብ ትግል ደጋፊ ሆነው ተሰየሙ። መርሻ ዮሴፍ በአራተኛው ጉባዔ ማን ወያነ በሰላም ይወርዳል አለ ብሎ ክዶ ዓቅዋሙን እንደካደው ሁሉ በዚሁም በአንጃው ስብሰባ 36ኡ ሁለገብ ትግል ስላሉ መርሻም አቅዋሙን ክዶ የሁለገብ ትግል ደጋፊ ሆነ። ይህ ግን ማድባት እንጂ ሌላ አለመሆኑን በአመራር ምርጫው ተጋልጥዋል። የችሎታው ነገር ይረሳና አቅዋም ስንል ለአንጃው አመራር የተመረጡት በሞላ ወደ ወያኔ እንግባ ባዮች ናችው። መስፍን ተፈራ፣ ለገሰ አጃቢ፣ መልካሙ፣ አለማየሁ፣ ጌታችው አየለ፣ ሰለሞን ወርቅነህ፣መስፍን ማርዮ፣ለይኩን፣አበበ ጽጌ፣ መሃመድ አህመድ፣መርሻ፣ታየ ዘገየ ገብረህይወት፣ ሁሉም ወደ ወያኔ እንግባ ባዮች ነበሩ፣ናችውም። ስለዚህም መርሻ በስብሰባው የብዝዎቹን አቅዋም የደገፈ ቢመስልም የራሱን ጀሌዎች በማሰለፍ ያው ወደ ወያኔ እንግባ አቅዋሙን ሊያስቀድም መዘጋጀቱ ግልጽ ነው። ሁለገብ ትግል የሚለው ውሳኔ ለሰላሙ ትግል መዋድቅ በሚል መታጀሉ አለምክንያት አይደለም።በዚሁ ተንኮል የተበሳጩት በየነ ጉራና ዮሃንስ የወያኔ ሰርጎገቦች ተብለው እየተወገዙ ናችው። በዚህ ሁሉ መሃል ተመክሮ ያላቸው እነ ሰለሞን ገብረስላሴ ከአመራር ሲወርዱ የ 70 አምቱ መርሻ

ግን ተለመንኩ በሚል ራሱ ባዘጋጅው የለምኑኝ ቀልድ አማካኝነት በአመራር ቦታ ቀጥልዋል። ከአመራር ይወርዳል ብሎም ከመርሻ በአቅዋም የተነሳ ይለያል ተብሎ የነበረው ጌታችው በጋሻው ግን ቢገርምም ከአዛውንቱ አንጃ ጋር መቀጠሉን መርጥዋል።

በአንጃው ጉባዔ የሚያስገርሙ ሁኔታዎች ተከስተዋል። የክፍሉ ታደሰ መልክት ላኪነት ብቻ ኣይደለም። እንግዳ የተባሉት ዶክተር ሙሉጌታ ስዩምና ወይዘሮ ፍቅርተ ድምጽ ስጡም ተብልዋል። ሁለቱም ገለልተኛ ሳይ/ሆኑ ከመርሻና አን/ጃው ጋር የተሰለፉ ናችው። ወደ ወያኔ አንገባም ካልን ዘንድ ከኢህአፓ እንታረቅ ያሉም ነበሩ። ይህ ግን የይስሙላ ለመሆኑ መረጃው እርቅ ያሉቱ ዋናውን ከፋፋይና በጥባጭ መርሻ ዮሴፍን መሪያችን ብለው ሲመርጡ ነው። ወደ ወያኔ ካልገባን ብሎ ድርጅትን የከፈለው መርሻ ተገልብጦ ሁለገብ ትግል ሲል ለምንስ ድርጅትን በአንጃ ሰነጠቅክ የሚለው አንድ ሰው እንዴትስ ይጠፋል ተብሎ መጠየቅ አለበት። የእነ ወይዘሮ ፍቅርተ ታረቁ ምክር ቀና ሊሆን ቢችልም የግጭቱ ምንጭ የአንድ ግለሰብ ቀቢጸ ተስፋ ነበርና ይህን ግለሰብ ያላሰወገደ ሂደት ዋጋ ቢስ መሆኑ ሊሳት አይገባውም። የአንጃው ስብሰብ ራሱ መርሻ ካጠመደበት የአፊዳቪት የመፈረም ውርደት የተላቀቀ አይደለም። መርሻ ሴራውን ቢሸርብም ለወያኔ እንደር መስመሩ ጊዜያዊ ሽንፈትን ተከናንብዋል። ነገ ግን ሌላ ቀን ነው። በተፈጠረ በአመቱ 5ኛ ጉባኤ ደረሰኩ ባዩ ቡድን ራሱን ቢደልልም ሃቁ ግን አንጃው ድርጅትን ከመጉዳት ሌላ ምንም አለመስራቱን ያሳያል።የመርሻ ዮሴፍ ቅሌት የተባለው በሽፍንፍን ቢያልፍም ለወጣቶች ቦታ እለቃለሁ ያለው መርሻ በመሪነት መቀጠሉ ያልተጠበቀ አልነበረም። የስልጣን ጥሜት ነውና ለዚህ ሁሉ ያደረሰው። ሆኖም የአንጃው መጨረሻ ደወል እየተደመጠ ነው። መሪ የተባሉት በአብዛኛው ከመርሻ ተከታይነት ውጪ ችሎታ አልባ ናችው። አንጃው ከተመሰረተ ጀምሮ ለጸረ ኢህአፓዎች የፓልቶክ መድረክ ከመስጠት ውጪ ይህ ነው የሚባል ስራ አልሰራም። ወደፊትም አይሰራም። ፍላጎትም ችሎታም የሉምና ነው። የአንድ አዛውንት መጫወቻ መሆኑ የመረራቸው ራሳችውን አግልለዋል፣ ወደፊትም ያገልላሉ። ትግል ፈልጎ በሌላ በኩል ደግሞ ጸረ ትግል ከሆነው መርሻ ዮሴፍ ጋር ተሰልፎ የሚገኝ ውጤት የለም።

ለትግል የተነሱ ከመርሻ ዮሴፍ አንጃ ይለዩ!!